# Why 3 Ha's (ሀ/ሐ/ኀ), 2 Sa's (ሰ/ሠ), 2 A's (አ/ዐ) and 2 Tse's (ጸ/ፀ)?

## የአማርኛውን ትርጉም ከግርጌ ያገኛሉ

Why Ethiopic has 3 Ha's (ሀ/ሐ/ኀ), 2 Sa's (ሰ/ሠ), 2 A's (አ/ዐ) and 2 Tse's (ጸ/ፀ)?

This is one of the most frequent questions we receive. It will be addressed briefly below.

Although, they are not properly used today, and some renowned Ethiopians (including the late Ato Haddis Alemayehu – Author of "Fiqir iske meqabir") went as far as suggesting to abolish the two Ha's, the one Sa, the one A, and the one Tsa, most Ethiopian language experts and authorities (like Aleka/Prof./ Kidane Wold Kifle, Aleka Desta Teklewold, Blata Mersaehazen Woldekirkos, Prof. Amsalu Aklilu, etc.) strongly disagree with the notion that these alphabets are "repeats" and they should be abolished. The latter contend that not only in shape, there are also differences in sound (and meaning to the word that particular syllabic alphabet is used) between the three Ha's, the two Sa's, the two A's and the two Tse's. You will find examples to the bottom of the page.

Because of that, we use different variants from each group for different words depending on the syllablic sound the word has. The details might be long. But to make the story short, some of the variants arise from the fact that Amharic inherited lots of words from Geez that are voiced completely different from how we voice them today. **ዓ** in **ዓይን** (Eye) is a very good example - it is a throat sound than the glotis. It is still used in throat sound in Tigrigna.

The other reason is that Amharic and most other languages that use the same alphabet stress (for emphasis) in syllabic alphabets depending on the word meaning and as a result the alphabet variant that is being used becomes different. Very good examples are **ኃ** in **ኃይል** ('Hail' – power/energy)፣ **ኃይለ-መለኮት** ('Haile-Melekot- Power of the Divine)፣ **ኃጢአት** ('Hatyat' – Sin)፣ **ኀፍረት** ('Hafret' – Shame/Shyness) and **ሠ** in **ንጉሥ** ('Nigus' – King), **ሠራዊት** ('Serawit' – Army)፣ **ሥራ** ('Sira' – Work) etc.). If you really give a close attention to these words, you will absolutely understand why the language (s) give emphasis to these words, and as a result the other variant (which is **ኀ** and **ሠ**) is used instead of **ሀ**(**ሐ**) and **ሰ**.

Sometimes, if you use the wrong alphabet for that particular word, not only the word sound, but also the meaning of the word completely changes. Here is a good example. **ሠረቀ** (meaning to emanate, as in the dawn of light) can totally change its meaning if it becomes **ሰረቀ** (meaning 'he steals'). Instead of **ሥ** if you write '**ስ'ነሥርዓት**, the meaning of the word totally changes as **ስነ** (meaning, Tooth), **ሥርዓት** (literally means, Order). There is no such word in Amharic to say the 'order of tooth'. Likewise **ምሁር** ('Mihur')፡- educated, expert; **ምሑር፡-** one who has been forgiven; **መሳሳት** ('Mesasat')፡- to err, make mistake; **መሣሣት፡-** to get thinner or handle something with extra caution; **መአት** ('Me'at')፡- many/multitude; **መዓት፡-** catastrophe; **ሳለ** ('Saala')፡- he coughs; **ሣለ**:- he draws; **ሠራዊት** ('Sarawit'):- army; **ሰራዊት**:- big divisions, colons; **ሕብር** ('Hibir'):- color; **ኅብር**:- collaborating, associated, organized; **አባይ** ('Abay'):- he/she who lies; **ዓባይ**:- big, Nile river; **በአል** ('Baal'):- idol of the Jews; **በዓል**:- special day, commemoration day; **አመት** ('Amat'):- servant; **ዓመት**:- year; **አራት** ('Arat'):- number 4; **ዐራት**:- sleep; **ትንሳኤ** ('Tin'sae'):- to forbid; **ትንሣኤ**:- to rise. The list continues.

Today you may not find many people writing following the rules, and may be not many readers recognize the differences. A very good reference we recommend to look into the correct usage of syllabic alphabets in words is the Amharic Bible published in 1962 during the reign of Emporor Haile Selassie. https://bible.org/foreign/amharic/

The important message is that, there is good reason that all the alphabets are maintained and it is good to teach and learn all the 34 alphabet families. But you may not need to bother much to learn the different sounds now until you progress in your lessons and you come to the point where you feel it is time to focus on these details.

However, it may be a good idea to give close attention which words take which particular alphabet in writing and sometimes to practice for yourself. This way the number of words you write correctly will grow by the day and you will be an expert in no time.

Following are the sound variations and some of the word examples for each of the variant syllabic alphabet from each group.

**ሀ** (**ሀሌታው ሀ**) – Sounds like HA

**ምሳሌ - ሀብት፣ ሀሌ፣ ሀያ፣ ሆይ፣**

**ሐ** (**ሐመሩ ሐ**) – Sounds like HHA (**ይጠብቃል**)

**ምሳሌ - ሐር፣ ሐመር፣ ሐሜት፣ ሐዋርያ**

**ኀ** (**ብዙኀኑ ኀ**) – Sounds like XA

**ምሳሌ - ኃይል፣ ውኃ፣ ኃይለመለኮት፣ ኃጢአት፣ ኅፍረት፣ኅብስት**

**ሰ** (**እሳቱ ሰ**) – Sounds like SA

**ምሳሌ - ሰዓት፣ ሰነፍ፣ ሰውነት፣ እሳት**

**ሠ** (**ንጉሡ ሠ**) – Sounds like SZA (**ይጥብቃል**)

**ምሳሌ - ንጉሥ፣ ሥራ፣ ሥርዓት፣ ሥልጣን፣ ሥጋ**

**አ** (**አልፋው አ**)- Sounds like A. It's Glottal (**የትናጋ ድምፅ**)

**ምሳሌ - አፍ፣ አየር፣ አገር፣ አንበሳ**

**ዓ** (**ዓይኑ ዓ**) – Sounds like A. But it's Pharyngeal (**የጉሮሮ ድምፅ**)

**ምሳሌ - ዓይን፣ ዓሣ፣ ዓላማ**

**ጸ** - Sounds like TSA

**ምሳሌ - ጸጉር፣ ጸሎት፣ ጸጥታ፣ጸም**

**ፀ** - Sounds like TZA (**ይጠብቃል**)

**ምሳሌ - ፀሐይ፣ ፅንስ (ፀነሰች)፣ ፀባዖት**

FHL PRODUCTIONS (2013)

# “ሞክሼ” ሆሄያት ለምን ያስፈልጋሉ? አጠቃቀማቸውስ?

**ከእምነት ተስፋና ፍቅር ዝግጅት ክፍል (፳፻፫ ዓ.ም)**

በተደጋጋሚ ከሚደርሱን ጥያቄዎች አንዱ “ሞክሼ” ሆሄያት (ሀ፣ ሐ፣ ኀ/ ሰ፣ ሠ/ አ፣ ዐ/ ጸ፣ ፀ) ለምን ያስፈልጋሉ? አጠቃቀማቸውስ? የሚል ነው። ጉዳዩ ሰፊ ቢሆንም በአጭሩ እንደሚከተለው መልስ እናቀርባለን።

ምንም እንኳን ዛሬ በአግባቡ ጥቅም ላይ እየዋሉ ባይሆንምና ክቡር አቶ ሐዲስ ዓለማየሁን ጨምሮ አንዳንድ ታዋቂ ኢትዮጵያውያን “ሞክሼ” ፊደላቱ አንዳቸው ብቻ ቀርተው ሌሎች መወገድ አለባቸው እስከማለት የደረሱ ቢሆንም የቋንቋ ተመራማሪዎችና በጉዳዩ ጥልቅ እውቀት ያላቸው ሊቃውንት (አለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ፣ አለቃ ደስታ ተክለወልድ፣ ብላታ መርስዔኀዘን ወልደቂርቆስ፣ ፕሮፌሰር አምሳሉ አክሊሉ ወዘተ) ደግሞ ይህን አጥብቀው በመቃወም ሲከራከሩ ኖረዋል።

ከኋላ የተጠቀሱት ሊቃውንት እንደሚሉት የፊደላቱ ልዩነት በምስል (ቅርጽ) ብቻ ሳይሆን በድምፅና የሚገኙባቸውን ቃላት ትርጉም በመቀየርም ስለሆነ ተጠብቀው መቆየትና ለትውልድ መተላለፍ ይኖርባቸዋል።

በዚህ ምክንያት እንደመነሻ ቃሉ (ሥርወቃሉ) ድምፅ ልዩነት ከእያንዳንዱ “ሞክሼ” ፊደል ተስማሚውን እንጠቀማለን ማለት ነው። ዝርዝሩ ረጅምና ለሊቃውንቱ የሚተው ነው። በአጭሩ ለማብራራት ያህል የእነዚህ ፊደላት የአጠቃቀም ልዩነት አንዱ ምክንያት አማርኛ፣ ትግርኛና ሌሎችም ሴማዊ ቋንቋዎች ብዙ ቃላት ከግእዝ የወረሱ መሆኑና ድምፃቸውም ዛሬ በአማርኛ ከምንጠቀምበት በተወሰነ ደረጃ ልዩነት የነበረው መሆኑ ነው። በ ‘ዓይን’ ውስጥ ያለው ‘ዓ’ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው - ዛሬ እንደተለመደው የትናጋ ድምፅ ሳይሆን የጉሮሮ ድምፅ ነው። በትግሪኛ ቋንቋ ዛሬም ይህን የመሰለ አጠቃቀም አለው።

ሌላው ምክንያት አማርኛና ሌሎችም ፊደሉን የሚገለገሉ ሴማዊ ቋንቋዎች ለአንዳንድ ለየት ያሉ ቃላት አፅንዖት ለመስጠት የሚገለገሉባቸው ፊደላት የተለዩ መሆናቸው ነው። የሚከተሉት ጥሩ ምሳሌዎች ይሆናሉ፡- ኃይል፣ ኃይለ-መለኮት፣ ኀጢአት፣ ኀፍረት በሚሉት ቃላት ውስጥ የሚገኘው ‘ኀ’፤ ንጉሥ፣ ሠራዊት፣ ሥራ በሚሉት ቃላት ውስጥ የሚገኘው ‘ሠ’። እያንዳንዱን ቃላት በቅርበት ከተመለከትናቸው ቋንቋዎቹ ለእነዚህ ቃላት ለምን አፅንዖት መስጠት እንዳስፈለጋቸውና ከ ‘ሀ’/’ሐ’ እና ‘ሰ’ ይልቅ ‘ኀ’ እና ‘ሠ’ ፊደላት በጥቅም ላይ የዋሉበት ምክንያት ግልጽ ይሆናል።

አንዳንድ ጊዜ ትክክለኛ ያልሆነውን ፊደል በመጠቀም ቃላት ሙሉ ትርጉማቸውን እስከመቀር የሚደርሱ መሆኑ ሌላው ጉዳይ ነው። የሚከተሉት ጥሩ ምሳሌ ይሆናሉ፡- ሠረቀ (ወጣ ማለት ነው - ሠረቀ-ብርሃን - ብርሃን ወጣ/መውጭያ እንደማለት)። ይህን ለማለት ፈልገን ‘ሰረቀ’ ብለን ብንጽፍ በተጠቀምንበት አንድ “ሞክሼ” ፊደል ምክንያት ትርጉሙ ‘የማይገባውን ወሰደ፣ ሌባ ሆነ’ ማለት ይሆናል። እንደዚሁ ሥነሥርዓት በማለት ፋንታ ስነ-ሥርዓት ቢጻፍ ‘ስነ’ ማለት (ከግዕዝ) ጥርስ ማለት ስለሆነ ትርጉሙ ይዛባል ማለት ነው። እዚህ ላይ ‘ሥነ’ የሚለው ቃል መገኛም ግእዝ መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል።

ምሁር፡- የተማረ፣ ሊቅ፤
ምሑር፡- ምሕረት (ይቅርታ) ያገኘ፤

መሳሳት፡- ትክክል ያለመሆን፤

መሣሣት፡- መቅጠን፣ ሥሥ መሆን ወይም በጥንቃቄ መያዝ፤

መአት፡- እጅግ ብዙ፤

መዓት፡- ቍጣ፤

ሳለ፡- በጉሮሮው ኡህ! ኡህ! አለ፤

ሣለ - ሥዕልን (ምስልን) ሠራ።

ሠራዊት፡- ወታደሮች፤

ሰራዊት፡- ዓምዶች፤

ሕብር፡- ቀለም፤

ኅብር፡- የተባበረ፤

አባይ፡- የሚዋሽ፣ የሚያብል፣ ቃሉን የሚለውጥ፤

ዓባይ፡- ትልቅ፣ ከፍ ያለ፣ የወንዝ ስም፤

በአል፡- አይሁድ ያመልኩት የነበረ የጣዖት ስም፤

በዓል፡- ልዩ ቀን፣ የተከበረ ቀን፤

አመት፡- አገልጋይ፤

ዓመት፡- 12 ወራት ከ 5/6 ቀን፤

አራት፡- ቍጥር፤

ዐራት፡- መኝታ፤

ትንሳኤ፡- መከልከል፤

ትንሣኤ፡- መነሣት፤ ዝርዝሩ ረዘም ያለ ነው።

በቤተክርስቲያን ትምህርት እያንዳንዱ ፊደል የተሰጠው የቍጥሮች ስያሜ ጉዳይ ደግሞ ሌላው የፊደላቱን እንደተጠበቁ የመቆየት አስፈላጊነት የሚደግፉ ወገኖች የሚያቀርቡት ተጨማሪ መከራከሪያ ነው።

በምሳሌ እንመልከተው። አብዛኛው የዓለም ቋንቋዎች ፊደላት (ላቲንን ጨምሮ) ድምፅን ብቻ ይወክላሉ። የግእዝ ፊደላት ከሌሎች የዓለማችን ፊደላት በተለየ አምስት ባሕሪያት አሏቸው። እነሱም ምስላዊነት (Pictography)፣ ፅንሰ-ሐሳባዊነት (Ideography)፣ ሥነ-ከዋክብታዊነት (Astrography)፣ ቍጥራዊነት

(Numerology)፣ የማያሻማ ድምፅ ወካይነት (Syllagraphy) ናቸው። ዝርዝሩ ሰፊ ቢሆንም በአጭጭሩ ለመግለጽ ያክል ምስላዊነት ፊደላቱ ነባራዊውን ዓለም የሚያንጸባርቁ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው። ለምሳሌ ‘በ’ ቤትን ወይም በርን፣ ‘ዐ’ ዓይንን ይመስላልና። እነዚህ የፊደላቱ ቅርጽ መነሻም እንደሆኑ ይጠቀሳል። ፅንሰ-ሐሳባዊነት ማለት ፊደላት ፅንሰ-ሐሳብን፣ በማኅበረሰብ ውስጥ ያለን ደረጃ ወዘተ የሚገልጹ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው። ለምሳሌ በ ‘ረ’ ውስጥ ፮/6ኛው ፊደል ‘ር’ ርዕስ፤ ራስ፣ መሪ፣ አለቃ፣ ርዕሰ-መንግሥት፣ መራሔ-መንግሥት፣ ርዕሰ-መኳንንት ወዘተ የሚለውን የሚያመለክት ነው። ሥነ-ከዋክብታዊነት የተባለው ፊደላት ለጊዜ (አመታትና ዘመናት) መቁጠሪያ ሆነው የሚያገለግሉ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው። ሃያ ስድስቱ መደበኛ የግእዝ ፊደላት በ ፯/7ቱ ብዜቶቻቸው በድምሩ ፻፹፪/182 ሲሆኑ ይህም የዓመት አንደኛው አጋማሽ (One Equinox) ይሆናል። በዚህ ምክንያት እያንዳንዱ ፊደል በሁለቱ የዓመት አጋማሾች (በዓመት ውስጥ) አንድ-አንድ ቀን ይወክላል ማለት ነው። ከዚሁ ጋር ፯/7ቱ የአንድ ቤት ፊደላት የሳምንቱን ፯/7 ቀናት ይወክላሉ። ቍጥራዊነት የተባለው እያንዳንዳቸው ፊደላት የሚወክሉት ቍጥር (ከ 1 እስከ 5600 ድረስ) መኖሩን የሚያመለክት ነው። እነዚህ ቍጥሮች ቃላት የተለያየ ምሥጢርን እንዲይዙ አድርገዋቸዋል። ለምሳሌ ‘አብርሃም’ በሚለው ቃል ውስጥ አ=፵/40፣ ብ=፱/9፣ ር=፮/6፣ ሃ=፩/1፣ ም=፬/4 ቍጥሮችን ይወክላሉ። እነዚህ ቍጥሮች ሲደመሩ ፷/60 ይመጣል። ይህንን ፷/60 ለፊደላቱ ቍጥር (፭/5) ብናካፍለው ፲፪/12 ይሆናል። ይህም ከአብርሃም የተገኙትን የእስራኤል ፲፪/12 ነገዶች የሚያመለክት ነው። ዶ/ር ለይኩን ብርሃኑ፣ “የግዕዝ መማሪያ” በሚለው መጽሐፋቸው እንደገለጹት ደግሞ ሊቃውንት ዳግማዊው አዳም እውነተኛው መሢሕ ኢየሱስ መሆኑን የተረዱት በፊደሎቹ አቀማመጥና መለያ ቍጥር ነው። ይኸውም አ(፵/40)፣ ዳ(፻/100)፣ ም(፬/4) = ድምሩ ፻፵፬/144 ይሆናል። በተመሳሳይ ኢ(፵/40)፣ የ(፺/90)፣ ሱ(፯/7)፣ ስ(፯/7) = ድምሩ ፻፵፬/144 አንድ ዓይነት ነው። ሊቃውንቱ “ሞክሼ ፊደላት” ይቀነሱ ማለት እነዚህ ቍጥሮችም ይቀነሱ ማለት ስለሚሆን በርካታ መፋለስ ያስከትላል የሚሉትም በዚህ ምክንያት ነው። በመጨረሻ የተጠቀሰው የማያሻማ ድምፅ ወካይነት የተባለው ሲሆን የግእዝ ፊደላት ላቲንን ጨምሮ ከአብዛኛዎቹ የዓለማችን ፊደላት በተለየና በላቀ ሁኔታ ለየትኛውም ዓይነት ድምፅ የማያሻማ ፊደል ያላቸው መሆኑን የሚያመለክት ነው። በዚህም ምክንያት ማንኛውም ሰው ፊደላትን ብቻ በማጥናት (ላቲንን በመሰሉ ፊደላት እንደተለመደው ሌላ ተጨማሪ ትምህርት ሳይሰጥ) ቃላትንና ጽሑፍን ያለምንም ስሕተት ለማንበብ ይችላል ማለት ነው።

አሁን አሁን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመዳከሙ የ “ሞክሼ” ፊደላት አጠቃቀም እየተረሳና ይህን ሕግ ጠብቀው የሚጽፉ ደራስያንና ልዩነቱን የሚገነዘቡ አንባቢያን እያነሱ መጥተዋል። ሆኖም በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመን በ1954ዓ.ም የታተመው መጽሐፍ ቅዱስ ለቃላት አጻጻፍ ጥሩ ማመሳከሪያ ሆኖ ሊያገለግል ስለሚችል በጥንቃቄ ተለቅሞ የተሠራውን ኮፒ በኢንተርኔት ላይ ለማግኘት የሚከተለውን ይጫኑ፡- https://bible.org/foreign/amharic/

ስለዚህ በዚህ ርዕስ ለማስተላለፍ የምንፈልገው ጠቃሚ መልእክት ሁሉም ፊደላት የቆዩልን በበቂ ምክንያት ስለሆነ ሁሉንም ፊደላት መማርና ማስተማር ተገቢ መሆኑን ነው። ይሁን እንጂ ልጆች ያሉበትን ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት ይህን ትምህርት ሊረዱ እስከሚችሉበት ዕድሜ ድረስ ማቆየት ይቻላል።

ወጣቶችና ጎልማሶች ግን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ ይልቁንም የአጻጻፍ ሥርዓቱን ትኩረት ሰጥተው ቢከታተሉት በየቀኑ አጣርተው የሚጽፏቸው ቃላት ቍጥር እያደገ በመሄድ በአጭር ጊዜ የአጻጻፍ ባለሙያ ለመሆን ይችላሉ።

የሚከተለው ዝርዝር በ "ሞክሼ" ፊደላት መካከል ያለውን የድምፅ ልዩነት ከቃላት ምሳሌዎች ጋር ያሳያል፡-

**ሀ** (**ሀሌታው ሀ**) – Sounds like HA

**ምሳሌ - ሀብት፣ ሀሌ፣ ሀያ፣ ሆይ፣**

**ሐ** (**ሐመሩ ሐ**) – Sounds like HHA (**ይጠብቃል**)

**ምሳሌ - ሐር፣ ሐመር፣ ሐሜት፣ ሐዋርያ**

**ኀ** (**ብዙኀኑ ኀ**) – Sounds like XA

**ምሳሌ - ኃይል፣ ውኃ፣ ኃይለመለኮት፣ ኃጢአት፣ ኀፍረት፣ኀብስት**

**ሰ** (**እሳቱ ሰ**) – Sounds like SA

**ምሳሌ - ሰዓት፣ ሰነፍ፣ ሰውነት፣ እሳት**

**ሠ** (**ንጉሡ ሠ**) – Sounds like SZA (**ይጥብቃል**)

**ምሳሌ - ንጉሥ፣ ሥራ፣ ሥርዓት፣ ሥልጣን፣ ሥጋ**

**አ** (**አልፋው አ**)- Sounds like A. It's Glottal (**የትናጋ ድምፅ**)

**ምሳሌ - አፍ፣ አየር፣ አገር፣ አንበሳ**

**ዓ** (**ዓይኑ ዓ**) – Sounds like A. But it's Pharyngeal (**የጉሮሮ ድምፅ**)

**ምሳሌ - ዓይን፣ ዓሣ፣ ዓላማ**

**ጸ** - Sounds like TSA

**ምሳሌ - ጸጉር፣ ጸሎት፣ ጸጥታ፣ጾም**

**ፀ** - Sounds like TZA (**ይጠብቃል**)

**ምሳሌ - ፀሐይ፣ ፅንስ (ፀነሰች)፣ ፀባዖት**

**ማጣቀሻ**:


1. **አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፤ "መዝገበ ፊደል"፣** 1927 **ዓ.ም**

2. **ሐዲስ ዓለማየሁ፤ "ፍቅር እስከ መቃብር"፤** 1958 **ዓ.ም**

3. **ዲ/ን ኀሩይ ባዬ፤ "፬ቱ ሞክሼ ሆህያት"፤ ስምዐ ጽድቅ ጥር ፯**/7፤2004 **ዓ.ም**

4. **ግርማ ጌታሁን፤ "በዐማርኛ ሥርዐተ-ጽሕፈት ውስጥ የድምፀ-ሞክሼ ሆሄያት አጠቃቀም ማስታወሻ"፤ ዓመተምሕረቱ ያልተጠቀሰ**

5. **ክንፈ ሚካኤል፣ "ስለ አማርኛ ፊደል መሻሻል የተደረጉ ጥናቶች መዘርዝር"፤** 2001 **ዓ.ም**

6. Scelta G.F (2001). The comparative Origin and Usage of the GE'EZ Writing System of Ethiopia.

7. **ዶ/ር ለይኩን ብርሃኑ** (1998 **ዓ.ም**)፣ **"የግዕዝ መማሪያ"**